Washington State Department of Labor & Industries
Division of Occupational Safety and Health

# የስራ ደህንነት እና ጤና መምሪያ (DOSH) የአደጋ ማስጠንቀቂያ

ሰራተኞችን ከስራ ቦታ አደጋዎች ለመከላከል መርዳት

ማርች 2021

## ከአውቶብስ አሽከርካሪዎች የትከሻ ጉዳት የሚያመጡ የደህንነት መከላከያዎች

ማሳሰቢያ፡ የአውቶብስ አሽከሪካሪዎች ቀጣሪዎች

### ለትከሻ ጉዳት መንስኤ የሚሆኑ ተጋጋሚ እንቅስቃሴዎች

በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ ለተለያዩ የትራንዝት ኤጀንሲዎች የሚሰሩ የአውቶብስ አሽከሪካሪዎች በተጋጋሚ በሚከፈትና በሚዘጋ በእጅ በሚሰራ ኦፕሬተር፣ ለኮቪድ-19 መከላከያ መንገድ የተተከሉ የደህንነት መከላከያዎች የትከሻ ጉዳቶች ስሜት ተጋልጠዋል፡፡

የአውቶብስ አሽከሪካሪዎች ወደ ጎናቸው፣ ከጀር በኩል በኋላ ሰውነታቸው ለመድረስ እና የደህንነት መከላከያዎችን ለማንቀሳቀስ ሀይል መጠቀም አለባቸው፡፡ ይህም የትከሻን መገጣጠሚያ ከሚገባው የመጨረሻ የእንቅስቃሴ ደረጃ እንዲደርስ ያደረጋል፡፡ ይህንን አስቸጋሪ እንቅስቃሴ በስራ ፈረቃ በሙሉ በተደጋጋሚ ማድረግ ደግሞ ከጊዜ በኋላ መገጣጠሚያን ይጎዳል፡፡ የእጃው እጅጌ በተለይም ለእንደዚህ ላሉ ተደጋጋሚ እንቅስቃሴዎች የተጋለጠ ነው፡፡

በአጠቃላይ የትከሻ ጉዳቶች በስራ ቦታ ከሚያጋጥሙ የከፉ አይነቶች ጉዳቶች አንዱ ነው፣ በዚህም በያንዳንዱ ተጎጂ ሰራተኛ በአማካይ ከአራት ወራት በላይ የስራ ሰዓትን ማጣትና ወደ $28,000 ጉዳት ያስከትላል፡፡  ለተጨማሪ መረጃ የ SHARP ን ህትመት ይመልከቱ- **www.Lni.wa.gov/safety-health/safety-research/files/2019/wmsdclaimssnapshot_shoulder.pdf**



በአውቶብሶች ላይ የደህንነት መከላከያዎችን ለማሰራት ስባል ወደ ጎንና ወደ ኋላ መድረስ፣ አሽከርካሪዎችን ለትከሻ ጎዳት አደጋዎች ያጋልጣቸዋል፡፡ የክንግ ካውንቲ ሜትሮ የፎቶ መልካም እርዳታ

### ጎዳቶቹን እንዴት እንከላከል

ተመራጩ መፍትሄ የደህንነት መከላከያዎችን ወደ አውቶማቲክ እንዲቀየሩ በማድረግ የአውቶብስ አሽከሪካሪዎቹ ተደጋጋሚ አስቸጋሪ እንቅስቃሴ ሳያስፈልጋቸው መክፈትና መዝጋት ይችላሉ፡፡ ይህም በትከሻ ላይ ጉዳት የሚደርሰውን እንቅስቃሴ ማስወገድ ብቻ ሳይሆን፣ በእያንዳነዱ መቆሚያ ላይ በትክክል ጥቅም ላይ ለማዋልም ይረዳል፡፡

በዚህ ደረጃ ወደ አቶማከትክ መቀየሩ የማይቻል ከሆነ፣ በእጂ ለሚሰሩ የደህንነት መከላከያዎች ጊዛዊ ማሻሻያ መድረግ ትችላለህ፤ እነሱም፡

- እጀታውን አሽከሪካሪውን የደህንነት መከላከያውን በመጠነኛ መንጠራራት ብቻ መክፈትና መዝጋት በሚያስችለው ስፍራ ያዛወሩት፡፡ መያዛውን አሽከርካሪው በቀላል መንገድ በእጃቸው በመያዝ በሚታላቸው፣ “በእጅ መጨበጥ” በሚችልበት ስፍራ በአግድሞሽ ቢያደርጉት፣ ያኑቱት፡፡
- ያልተገባ መንጠራራት እና አስቸጋሪ እንቅስቃሴን ለማስወገድ ለመከላከያው ማንጠልጠያ በማበጀት አንደጃውን ጫፍ ለአሽከርካሪው ቅርብ በሆነ ቦታ ይስቀሉት፡፡
- የደህንነት መከላከያው መያዣ ቢበጅለት ወቅት ደግሞ ማግኔት ወይም ሌሎች የደህንነት መከላከያዎች እንዲሰሩ ተገቢውን ሀይል እንዲፈልግ የሚያደርጉ ዘዴዎች በትክክል መኖራቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡




ይህንን የመሰሉ አውቶማቲክ የሆኑ የደህንነት መከላከያዎች፣ የትከሻን ጎዳት ሊከላከሉ ይችላሉ፡፡ ይህንን አይነቱ የደህንነት መከላከያዎች እንዴት እንደሚሰሩ ለማየት፣ ይህንን ቪዲዩ ይመልከቱ፡ **www.youtube.com/watch?v=_O52f_g6Oag**፡፡ የክንግ ካውነቲ ሜትሮ የፎቶ እና ቪዲዩ መልካም እርዳታ፡፡

## ሌሎች ማግኘት የሚችሉት ሀብቶች

የዚህን የአደጋ ማስጠንቀቂያ ኤሉክትሮኒክ ከኮፒ ለማግኘት፣ ወደ **https://www.lni.wa.gov/HazardAlerts**

የሰራተኛና እንደስትሪ (L&I) የደህንነት ደረ-ገፅ፡ **https://www.lni.wa.gov/safety-health/**

ለሌሎች ተያያዥ ህጎች፣ የአካባቢዎን የ L&I ባለሙያ ያግኙ ወይም የደህንነት ህጎች ድረ ገፅን ይጎብኙ፡ **https://www.lni.wa.gov/SafetyRules**

በቅርበት የሚገኝ የ L&I ቢሮን ለማግኘት፣ **https://lni.wa.gov/agency/contact/#office-locations**ን ይጎብኙ፡፡

### ከሰራተኛና እንደስትሪ እንዴት ነው እርዳታ ማግኘት የምችለው?

የሰራተኛና እንደስትሪ መምሪያ ውይይቶችን፣ ስልጠናዎችን እና የቴክንክ ድጋፎችን ከክፊያ ነፃ ለሰራተኞች ያቀርባል፡፡ ነፃ እና ሚስጥራዊ ምክክር ለማድረግ ዛሬውኑ በመደወል ቀጠሮ ይያዙ ወይም ለተጨማሪ መረጃ ወደ **www.Lni.wa.gov/SafetyConsultants** ይሀዱ፡፡

እንዲሁም በ 1-800-423-7233 ላይ መደወል ይችላሉ ወይም የአካባቢዎን የሰራተኛ እና እንዲስቱሪ ቢሮ በመጎብኘት ለ ምክር አስረዳደርን ይጠይቁ፡፡

*ይህ ማስጠንቀቂያ ቃጣሪዎችን፣ የሰራተኞች ቡድንን እና ተራተኞች ከስራ እንቅስቃሴያቸው ጋር በተገናኘ ሊከሰቱ ለሚችሉ ጉዳቶች ላይ ለማሳመስብ ተብሎ በሰራተኛ እና እንደስትሪ ክፍል የስራ ደህንነት እና ጤና መምሪያ(DOSH) የተዘጋጀው ነው፡፡ ይህም ደንብ አይደለም እንዲሁም አዲስ የህግ ግዴታዎችንም አላስቀመጠም፡፡ የቀረቡት መረጃዎችም የሚያካትቱት፤ የስራ ቦታ አደጋዎችን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ላይ ሀሳብን በማቅረብ እና ጠቃሚ አስገዳጅ የደህንነት እና የጤና ህጎችን አትቷል፡፡ እንዲሁም ለተጨማሪ መስፈርቶች እርስዎን ተያያዥ ህጎችን እንዲመለከቱ የስራ ደህንነት እና ጤና መምሪያ(DOSH) አስተያየት ሰቷል፡፡*

FY21-241 (Amharic) [03-2021]